# እንትን…



እንትናና እንቶኔ ምለው ተማምለው፣
በጠራራ ፀሓይ እንትን ተባብለው፣
ለኣድባር ኣውጋር መጀን ስለቱን ተስለው፣
ከእንትን ወረዱና ቶሎ ተቻኩለው፣
እንትን እያላቸው ዘመድ ኣዝማድ ሁሉ፣
ከእንትን ውስጥ ገቡና እንትን፣ እንትን ሲሉ፣
እንትኑ ጠፍቷቸው እንዲያ ሲዋልሉ፣
የእንትኑ መያዣ ተሰበረ ቅሉ፣



እንትኑ ሲደፋ ከእንትኑ ላይ፣
እንትኑም ፈሰሰ… ኣዬ! ኣዬ! እዬ!
"ምን ነካህ እንትና? ዓይንህም ኣያይ!
"እንትኑን ከእንትን ላይ ኣትሰቅለውም ወይ?"
ብላ ተቆጥታ እንትንም እያለች፣



በንዴት ብስጭት እንትን ብላ ዓበድች፣
እንትኗን ከእንትዋ እያደገደገች፣
ከእንትን ምንጭቅ ኣድርጋ እንትኗን ወሰደች።
በጠራራ ፀሓይ እንቶኔና እንትና
እንትን ተባብለው ጀምረው በደህና
እንትን ሲሉ ነበር በእንትን ጉዳና
እንትን ሆኖ ቀረ፣ ያውና! ያውና!

ገ/ኢ. ጎርፉ።